# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# መልከ መልካሙ ሞኝ ንጉስ

ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest; Alastair Paterson
ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው): Lyn Doerksen
የተተረጎመው: Henok Estifanos
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada

©2021 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



የእስራኤል ፈራጅ እና መሪ የሆነው ሳሙኤል አረጀ፡፡በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የእርሱን ስፍራ ተረክበው ያገለግሉ ዘንድ ሁለቱ ልጆቹን በእስራኤል ላይ ፈራጅ አደረጋቸው፡፡ነገር ግን የሳሙኤል ልጆች ምናምንቴዎች ነበሩ፡፡ገንዘብ ይወዱ ነበር፤ስልጣናቸውን ገንዘብ ለማግኘት በተሳሳተ መንገድ ይጠቀሙበት ነበር፡፡




ከልጆቹ ሐጢአት የተነሳ የእስራኤል ህዝብ ይሰቃይ ነበር፡፡በፍርድ ቤት የነበረው የፍርድ ሁኔታ ትክክል አልነበረም፡፡ ህዝቡ እርዳታ በፈለገ ጊዜ ለሳሙኤል ልጆች መክፈል ነበረባቸው፡፡ አንድ ነገር መደረግ ነበረበት፡፡ አንድ ቀን፤የእስራኤል ሽማግሌዎች በአንድነት ተሰብስበው፤ሳሙኤልን እርዳታ ጠየቁት፡፡
3


"በእኛ ላይ ይነግስ ዘንድ ንጉስ አንግስልን" ብለው ሽማግሌዎች ጠየቁ፡፡ የሳሙኤል አመጸኛ ልጆች በእነርሱ ላይ እንዲፈርዱ አልፈለጉም ነበርና፡፡ በዓለም ላይ እንዳሉ ሃገሮች ሁሉ እነርሱም ንጉስ ፈልገው ነበር፡፡
4


ሳሙኤል ተናደደ፡፡እስራኤል ንጉስ አለው! ኃያሉ ዘለዓለማዊው እግዚአብሔር እስራኤልን ገዝቷል፡፡ከረጅም ጊዜ በፊት፤እርሱ ከግብጽ ባርነት ነጻ አወጣቸው፤ያመልጡም ዘንድ ቀይ ባህርን ከፈለላቸው፡፡ ለእስራኤልም መልካም የሆነ ምድርን ሰጣቸው፡፡
5


ሳሙኤልም በጸለየ ጊዜ፤እግዚአብሔርም "የናቁት አንተን አይደለም፤ነገር ግን በእነርሱ ላይ እንዳልነግስ እኔን ንቀውኛውል፡፡እነርሱ ጣዖታትን እያገለገሉ ነው፡፡ድምጻቸውን ስማ እና ንጉስ አንግስላቸው" አለው፡፡
6


እግዚአብሔር ለሳሙኤል ምድራዊ ንጉስ ገንዘባቸውን በግብር እንደሚወስድ፤ እርሻቸውን እና የወይን መጥመቂያቸው እየወሰደ ራሱን እንደሚረዳ፤ ወንድ ልጆቻቸውን የጦር ሰራዊት ይሆኑ ዘንድ እንደሚያዛቸው፤ እና ሴት ልጆቻቸው ለእሱ ይሰሩ ዘንድ እንደሚያዝ ለህዝቡ አስጠንቅቃቸው ብሎ ነገረው፡፡
7


የንጉስ ወይን እርሻ
ጠብቅ
ነገር ግን ህዝቡ ንጉስ እንዲነግስላቸው ፈልገው ነበር፡፡
8


እግዚአብሔር ሳሙኤልን ወደ አንድ መልከ
መልካም፤አይን አፋር እና በጣም ረጅም ወደ ሆነ
ወጣት ልጅ መራው - ከየትኛውም ሰው ይልቅ ረጅም
ነበር። ስሙ ሳኦል ይባል ነበር።
ሳሙኤል ሳኦልን ባየው
ጊዜ፤እግዚአብሔር እንዲህ
አለው "በህዝቤ ላይ
የሚነግሰው ይህ ነው።"
9


በመታዘዝ፤ሳሙኤል ሳኦልን
የእስራኤል ንጉስ አድርጎ
ቀባው።ሳኦልን ለህዝቡ
ባቀረበ ጊዜ "ሺ ዓመት
ንገስ!" እያሉ ጮኹ።
10


ወዲያው ንጉስ ሳኦል ተፈተነ።እስራኤልን የሚጠሉ አሞናውያን፤የእስራኤልን
ከተማ ከበቡ፤የሁሉንም ቀኝ ዓይን በማውጣት አስፈራሩ።ምን አይነት ጨካኝ
የሆነ አቅድ ነው! የማስፈራሪያው ዜና ለንጉሱ ሳዖል ደረሰ።እርሱም ሰራዊቱን
ዝግጁ አደረገ።
11


ሁለቱም ሰራዊቶች
በተገናኙ ጊዜ፤ሳዖል
አሞናውያንን
አጠፋቸው፤እናም
ከተማይቱን አዳነ።ንጉስ
ሳዖል ለእግዚአብሔር
ክብር ሰጠ፤እንዲህም
እያለ ". . . ዛሬ
እግዚአብሔር በእስራኤል
ላይ መዳን አድርጓል!"
12


እግዚአብሔር በዚያን ቀን ለሳዖል ታላቅ የሆነ ድል ሰጠው።ነገር ግን
ሳዖል ሁልጊዜ እግዚአብሔርን አላከበረም።እንድ ቀን ፊሊስጤማውያንን
በጦር ከመግጠሙ በፊት፤ሳዖል ለእግዚአብሔር መስዋዕት አቀረበ። እርሱ ያ
የሳሙኤል ስራ እንደሆነ ያውቅ ነበር።
ሳሙኤል መጥቶ መስዋዕቱን እስኪሰዋ
ድረስ መጠበቅ እንዳለበት
እግዚአብሔር እንደሚፈልግ
ያውቃል። ነገር ግን ሳኦል ግን
እግዚአብሔርን አልታዘዘም!
13


ሳሙኤልም በደረሰ ጊዜ፤ሳዖልን "በሞኝነት አድርገኸዋል።የጌታ
እግዚአብሔርን ቃል አልጠበክም።አሁን የአንተ መንግስት አይቀጥልም"
አለው። ሳኦል ትንሽ ሐጢአት እንደነበር ሊያስብ የችላል።ነገር ግን
እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ሁልጊዜ
ከባድ ነገር
ነው።
14

በሌላ ጊዜ፤እግዚአብሔር የዓማሌቅ ሐጢአተኛ ሰዎችን እንዲያጠፉ ሳዖልን አዘዘው፡፡ ነገር ግን ሳዖል እና ህዝቡ የዓማሌቅን ንጉስ አጋግን በህይወት ተዉት፡፡ እነርሱም የከበሩ ነገሮችን፤በጎች እና በሬዎችን ሳይገሏቸው ማረኳቸው፡፡ ሳዖልም እነዚህን ለእግዚአብሔር መስዋዕት ይሆኑ ዘንድ ማርኳቸው አለ፡፡



15

ሳሙኤልም ሳዖልን "መታዘዝ ከመስዋዕት ይበልጣል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና፤እግዚአብሔርም የእስራኤል ንጉስ እንዳትሆን ንቆሃል" አለው፡፡ ሳዖልም በሰራው ሐጢአት በጣም አዘነ፡፡ነገር ግን በጣም ዘግይቶ ነበር፡፡ ቀሪው ሕይወቱ ደስታ አልነበረውም ምክንያቱም እግዚአብሔርን አልታዘዘምና፡፡



16

መልከ መልካሙ ሞኝ ንጉስ

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

1 ሳሙኤል 8-16

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

17





18 60

18

**ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።**

**እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።**

**ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት**
**ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።**

**በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር!** የሐ. 3.16

19